# Union of Tigreans in North America (UTNA)
## ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማተሰኣ)

UTNA
P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
UTNA67@verizon.net

Tel. (202) 265-8702
Fax. (202) 265-8703

05/02/2009

# የአገራችንን ሰላምና እድገትን ለመግታትና ለማደናቀፍ የሚጥሩ ሁሉ መጨረሻቸው ውድቀት ነው!!

## ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ህዝብ አስከፊውና ግፈኛው የደርግ ስርዓት ከስረ መሰረቱ ለመጣል ሁለንተናዊ መራራ መስዋእትነት ሲከፍል በምትኩ ከጫፍ ጫፍ ያሉት ህዝቦቿ በእኩልነት፣ መከባበርና መተጋገዝ የተመሰረተ አንድነትን ይፈጥሩ ዘንድ አስተማማኝ ሕገ-መንግስት በመቅረፅ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ባለበት እንዲሁም ለረዥም ዘመናት ከትውልድ ትውልድ እየተንከባለለ የመጣውን ድህነት በማጥፋት የኢኮኖሚ እድገት መልካም አርአያ ለመሆን የምታደርገው እልህ አስጨራሽ ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታየ ያለውን ለውጥ የዓለም አቀፍ ተቋማት ምስክርነታቸውን በሰጡበት ወቅት

- የአገራችን ህዝብ የአኗኗር ደረጃ እየተሻሻለና ስልክ፣ መብራት፣ መንገድ፣ ውሃ፣ ሕክምናና ትምህርት በከፍተኛ መጠንና ብሎም ጥራቱ እየታየ ማሻሻያ በሚደረግበት፣
- የአገራችን አስተማማኝ ሰላም የውጭ ባለሃብቶች በብዛት እንዲጎርፉ ምኽንያት ሆኖ የስራ አጥነት ደረጃ እየቀነሰ በሚሄድበት ባጠቃላይ የአገራችን ብሩህ ተስፋና ራእይ ኣበረታችና መልካም ጅማሮ በሚታይበት ወቅት ሰሞኑን ራሱን ግንቦት 7 ብሎ የሰየመ ተቃዋሚ ድርጅት

ሀ. የአገራችንን ሰላም ለማደፍረስ፣ ፀረ ህዝብ ተግባር ለመፈፀም፣ ሽበራን ለመፍጠርና የአገሪቱ የላቀ እውቀት፣ ሃብት ጊዜና ጉልበት የፈሰሰባቸውን የህዝብ ተቋማት ለማውደም፣

ለ. ያገሪቱ ከፍተኛ አመራር አካላትን ግድያ ለመፈፀም፣

ሐ. በየአከባቢው ተቀጣጣይ ፈንጆች በማጥመድ ህይወትና ንብረትን ለማጥፋት አልሞ በሚስጥር ሲንቀሳቀስ ረዥም ርቀት ሳይሄድ በኢትዮጵያ የፀጥታ ሃይሎች ጥበብና ብቃት በተሞላበት አኳኋን ያሰበው ሳይሳካ ቀድሞ በቁጥጥር ስር በማዋሉ የተሰማንን ኩራት፣ ደስታና ልበ ሙሉነት በሰሜን አሜሪካና ካናዳ ኗሪ በሆነው የትግራይ ተወላጅና በማህበሩ አባላት እንዲሁም ሰላም፣ ልማት፣ እድገት፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ወዳድ በሆነው ኢትዮጵያዊ ስም እየገለፅን

1. የግንቦት 7 ድርጅት አመራር ሰላማዊ የትግል ስልትን በመጣል ሽብርተኝነትና አጥፊነትን እንደ ዋና ዓላማ በመያዝ ኗሪነታቸው በውጭ ሃገር በማድረግ ኑሮውን ለማሻሻልና ልማትን ለማረጋገጥ ደፋ ቀና የሚለውን የአገር ውስጥ ህዝብ ቤንዚን እያርከፈከፉ እሳት ውስጥ እንዲማገድ እየገፉ

ራሳቸውን ሳያስነኩ ዳር ሆነው በህዝብ እልቂት የሚሳለቁ በሙሉ መንግስት ተገቢ ነው በሚለው መንገድ በሕግ የሚጠየቁበት ሁኔታ እንዲያመቻች፣

2. የተሰጣቸውን የህዝብና የመንግስት ሃላፊነትና አደራ በመካድና ወደጎን በመተው በፀረ ሕዝብ ተግባር ተሰማርተው መጥፎ አርአያ ለሆኑት የመንግስት ሹመኞችና ግለሰቦች ላይ መንግስት ተገቢና ለሌላው አስተማሪ የሚሆን እርምጃ እንዲወስድ፣
3. በመላው ክፍላተ ዓለም በተለይም ደግሞ በሰሜን አሜሪካና ካናዳ የሚገኝ የአገራችን ኢትዮጵያ እድገት፣ ልማት፣ ሰላም፣ ፍትህና ዴሞክራሲን መልካም ራእይ ያለው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በሙሉ በህይወት ሲኖር ዞሮ መግቢያው የሰላም፣ የፍቅር፣ የመልካም ባህል መገኛ ፣ የብዙ ብሄር ብሄረሰብ ውህደትና አንድነት ተምሳሌት ሆና ማየት የሚፈልግ በህይወት ሳይኖር ደግሞ መቀበርያው ክብርት መሬት መሆኗን የሚያምን ሁሉ የአገራችንን ሁለንተናዊ እድገት የሚፈታተኑና በሽበራ ተግባር የተሰማሩትን ክንዱን አስተባብሮ በያለበት እንዲታገላቸው በሰሜን አሜሪካ የትግራይ ተወላጆች ማህበር ስም ጥሪያችንን እያስተላለፍን በዚህ አጋጣሚ የአሸባሪዎች አደጋ ለማምከን በሚደረገው ርብርብ ዓቅማችን የፈቀደው ሁሉ ለመፈፀም በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ጎን እንደምንሰለፍ በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

ውድቀት ለፀረ ህዝብና አሸባሪዎች!!

በሰሜን አሜሪካ የትግራይ ተወላጆች ማህበር
ዋና ፅ/ቤት
ሜይ 02/2009